# የሶሴፐ አሊ ሁሴን የማያቆም የሰበዓዊ መብት ትግል

ጀንበሬ
አክቶበር 2016

በኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው ግፍ፣ ጭቆና፣ ባጠቃላይ ስለሰብዓው መብት ጥሰትና ዋልጌነት አጋጣሚው በፈቀደው ቦታና ሰዓት ሁሉ ሳይታክት ለዘመናት እየተሟጎቱ፣ እያጋለጡና ድምጽ አልባ ለሆኑት የሕሊና እስረኞች ሙሉ ድምጽ በመሆን ላይ ያሉት የኢትዮጵያ ፓለቲካ እስረኞች ኮሚቴ  ማለትም የሶሴፕ ፕሬዚደንት አቶ አሊ ሁሴ  ዛሬም ድንቅ ስራ በመስራት ላይ  ይገኛሉ። ሶሴፐ ድንበር፣ ዘር፣ ሃይማኖት፣ ጾታ፣ ፓለቲካ ተጽዕኖ ሳይበግረው የሰብዓዊ መብት ሙግትናውን በየትም ቦታ ለተጨቆነ ሰው ሁሉ መብት መከበር ይታገላል። ለዚህም ነው "**በየትኛውም ቦታ የሚሰራ ኢሰብዓዊ  ድርጊት በሌላውም አካባቢ ቢሆን ኢሰብዓዊ ድርጊት ከመሆን አያመልጥም**"።"  - ማለትም በኢትዮጵያ የሚካሄደውን ኢሰብዓዊ ድርጊት ብቻ በመኮነን በሌላ አገር ለምሳሌ በኤርትራ ውስጥ የሚካሄደውን ግፍ እንዳላዩ ማለፍ ትክክል አይደለም።

በነገራችን ላይ በየወሩ ከምድረ ኤርትራ ከ4 እስከ 5 ሺህ ወጣቶች ግፍን በመሸሸ እየተሰደዱ ይገኛሉ። ከፋሺስቱ መንግስታቸው ተርፈው ገሚሱ የበርሃ ቀለብ ሆኗል። በረሃውን ለመዝለቅ የቻሉት በውቅያኖስ ሰጥመው አልቀዋል። ዛሬ ከወያኔ ነጻ ሊያወጣን የሚሰብከን አንድ ቡድን ሻቢያን ዲሞክራሲያዊ መንግስት ነው ሲለን መሪውን ኢሳያስን ደግሞ ከፈጣሪ ቀጥሎ ቸርና መሃሪ መሪ አድርጎ ይቀባዋል'። ሻቢያ፣ ኢሳያስም፣ ወያኔም ባንድ የአምባገነን ጥላ ስር ያሉ ፋሺስቶች ናቸው። የኢትዮጵያን ግፍ ስናወግዝ የሻቢያውን መማር የለብንም። የሶሴፐም ትግል መስፈርቱ ይህ ነው።

የሶሴፐ  ፕሬዚደንት የሆኑት ስመጥሩ አቶ አሊ ሁሴን ሰብዕዊ መብትን አስመልክተው የሚያካሄዱት ከፍተኛ አስተዋጾያ ከፍተኛ ምስጋና የሚያጎናጽፍላቸው ቢሆንም አቶ አሊ ግን ምንም የተለየ ስራ አልሰራሁም በማለት በየቀኑ ድምጻቸው ለታፈነ የሕሊና እስረኞች ሳይታክቱ ድምጽ ሆነው ማስተጋባቱን ይወዱታል። ሶሴፐ ካሰራረቱ ጅምሮ በኢትዮጵያና በሌላውም አካባቢ ስላለ የሕዝቦች መብት ጥሰት ያቅሙን ለማበርከር፣ በወያኔ መሰሪ ሴራ ተይዘው ደዝባቸው ለጠፋ የሕሊና - የፓለቲካ፣ የሃይማኖት፣ የጾታ  . .  ወዘተ አስረኞች ሳይታክት ለመሟገት፣ በተለያዩ የዓለም ዙሪያ ተሰደው ለሚሰቃዩ ኢትዮጵያውያን ፍትህ ለማስገኘት ..  ይህ ነው የማይባል ከፍተኛ አስተዋጾ አድርጉኣል። ውጤትም አስመዝግቧል።




ኢትዮጵያዊው ፈይሳ ላሊሳ

ይህ ወጣት ገና ከጠዋቱ በለስ የቀናውና ድህነት ሳያሳቅቀው ያለውን በመብላት ለዘመናት መኖር ይችላል። ከወገኔ ውጭ ሃብቱ አመድ ይሁን በማለት ታላቅ መስዋዕትነትን የሚጠይቀውን የሰላማዊ አመጹን በምልክት አሳያቸው። ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብም የፈይሳን ዓላም በመከተል ዛሬ ከጽንፍ አስከ አጽናፍ ከኢትዮጵያውያን ዘልቆ ደጋፊ የአለም ሕዝብ ድጋፍ በመያዝ ላይ ነው። የዊኒፔግ ዮኒቨርሲቱ ተማሪዎችን ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል'።

የሶሴፑ ፕሬዚደንት አቶ አሊ  በማኒቶባ የዊኒፔግ ከተአማ ኗሪ ሲሆኑ በዚህ ከተማ ኑዋሪው ሕዝብ ስለ ኢትዮጵያ ሊያውቅ የሚገባውን በማሳወቅ የድርሻቸውን አድርገዋል በማድረግም ላይ ሲሆኑ ወደፊት ይህ ተግባራቸውን የሚገታው ሃይል አለመኖሩንም ይታያል። አቶ አሊ ሁሴን በክርስትናና በእስልምና ተከታይ ኢትዮጵያውያን ዝንድ ልዩ አድናቆት ያላቸው የሰበዊ መብት ታጋይ ምስል ናቸው። ዊኒፔግ የበርካታ አቦጂናል - የመጀመሪያዎቹ ባለመብት ኗሪዎች - ቦታ ብትሆንም የተገላቢጦሹ ሆኖ ልክ እንደ አሜሪካኖቹ ቀይ ሕንዶች የተረሱ ዜጎች የሚታዩባት ናት። በርካታ ስደተኞችም ያሉባት ከተማ ናት። ሶሴፓ የተለያዩ የስብዓዊ ድርጅቶችን በማሰባሰብ በዚች ከተማ ጠንካራ የሰብዓዊ መብት የጋራ ሕብረት እንዲመሰረት አድርጉኣል።

ስለሰብዓዊ መብት ባጠቃላይ በተለይም ባሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ስላለው የሰበዓዊ ጥሰት ሶሴፓ በየትምህርት ቤቱ፣ በኮሌጆችና በዩኒቨርርሲቲዎች ትምህርታዊ መግለጫዎችን ለተማሪዎች ያቀርባል። በዚህ ወር አቶ አሊ በዩኒቨርሲቲ ኦፍ ዊኒፔግ በመገኘት ለተማሪዎች ስለኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ ትምህርት በመስጠት ተማሪዎቹ ልክ እንደ ፈይሳ ላሊሳ እኛም ስለ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን መታሰራችንንና ፍትህ መፈለጋችንን ለመላው አለም ሕዝብ እናሳውቃልነ በማለት መስከረዋል።




**አኛም የዊኒፒግ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች  እንደ ፈይሳ ላሌሳ ለኢትዮጵያ ወገናችን እንቆማለን በማለት ድጋፍ ሰጥተዋል።**

ሴፐና ፕሬዘዳንቱ አቶ አሊ ሁሴን ለሚያደርጉት ታላቅ ስራ ማበረታቻ ይሆን ዘንድ ግሎባል ኮሌጅ የተባለው የተለያዩ ጥምር ድርጅቶችን ማለትም  የሮታሪ፣ የወርልድ ፒስ ፓርትነር፣ የካናዲያን ሙዚየምና የዊኒፔግ ፋውንዴሽን ልዩ ሽልማት አበርክቶላቸዋል። አቶ አሊ ሁሴን




በስማቸው ሽልማት ወይም ሙገሳ ሲደረግላቸው ምስጋና ማቅረባቸው ተገቢ ቢሆንም ለሳቸው ግን መመስገና ያለበትና መሸለም ያለበት ሶሴፓ ነው የሚል ጽኑ እምነት አላቸው። ይህን ዓይነት ክቡር የሆነ እምነት የታደሉት የዚያ ትውልድ እንቁ በመሆናቸው ስለመሆኑ አጠያያቂ አይሆንም።



ይህ ታላቅ አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሙዚየም የሚገኘው በዊኒፔግ ከተማ ሲሆን ተመርቆ ለሕዝብ ክፍት የሆነው ሴፕቴምበር 2014 ነው። ሙዚየሙ ከ400 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጭ ፈጅቷል። በዚህ ሙዚየም ውስጥ የሆሎኮስት ፍጅት፣ የአፓርታይድ ግፍና የማንዴላ ትግል . . .  ወዘተ ለሕዝብ በሚታዩበት ቦታ ሶሴፕም ከፍተና ተጋድሎ በማድረግ የቀይ ሽብርን እልቂት የሚያሳይበት ቦታ በማግኘት ይህን አስከፊ ታሪክ ያልሰማ እንዲሰማ፣ ያላየ እንዲያይ በማድረግ በተለይም ይህ አይነት ግፍ በምንም መንገድ በየትም አገር በማንም ሰው ላይ መደገም የለበትም የሚል ትምህርት ለወጣቱ ትወልድ በማስጨበጥ ላይ ነው።

ስለ ሰብዓዊ መብት የሚታገል ሁሉ ለዘላለም ይኑር!